ለክቡር አቶ ሺፈራው ሽጉጤ
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
በግብርናና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር ሚኒስትር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 48 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 35 ገጽ የሂሳብ መግለጫዎች በድምሩ 83 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡ ፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር!

ሰለሞን መብራቱ
የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ለተወካዮች ምክር ቤት የተላከው የሂሳብ መግለጫዎችን አይጨምርም፡፡

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት በፋይናንስ አዋጁ፣ ደንቡ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሰረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው ።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዓለም አቀፍ ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው።

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል።

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ መዛባቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ፣ አጥጋቢ ማረጋገጫና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል። ይሁን እንጂ በሪፖርቱ ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ይሁን የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ

ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም። ለኦዲቱ ሥራ መሰረት የሆኑት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው።

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን ወስዶ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተዘጋጁ የሂሳብ መግለጫዎች፡-

- የሂሳብ ማመዛዘኛ ማጠቃለያ፣
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ማጠቃለያ ሪፖርት፣
- የካፒታል ወጪ ሂሳብ ማጠቃለያ ሪፖርት፣
- የውስጥ ገቢ ወጪ ሂሳብ ማጠቃለያ ሪፖርት፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የ2009 የሂሣብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ብር ተሰብሳቢ ሂሳቦች በደንቡና በመመሪያው መሰረት የሚወራረዱ መሆኑ ሲጣራ፡-

   1.1. <u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ</u>

   - ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 858,524.01፣
   - ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 8,155,809.13፣
   - ከአምሰት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 16,453,996.40፣

- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 4,924,491.29፣

1.2. በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 249,683.00፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 16,567,071.34፣
- ከአምስት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 14,336,867.59፣
- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 26,040,684.07፣

1.3. በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 184,444.73፣
- ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 507,217.05፣
- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 232,681.10፣

1.4. በአርጳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 62,582.88፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 81,428.77፣

1.5. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 7,172.95፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 12,910.00፣
- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 3,767.40፣

1.6. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ ብር 183,059.73፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ ብር 688,949.97 ፣

1.7. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 685,171.88፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 458,370.46፣

በድምሩ ብር **90,694,883.75** በደንቡና በመመሪያው መሰረት ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን ስለሁኔታው ከ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ጀምሮ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ እንዲወራረዱ፤ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ሂሳቡ ሳይወራረዱ (ሳይሰበሰቡ) የሚገኙ መሆኑ፤

2. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ተከፋይ ሂሣቦቹ በወቅቱ የሚከፍሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

2.1. <u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ</u>

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 629,127.98፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 2,105,369.67፣
- ከአምስት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 638,919.18፣
- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 1,166,890.22፣

2.2. <u>በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>

- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 1,231,264.28፣
- ከአምስት በላይ እስከ አሥር ዓመት ድረስ የቆየ ብር 12,089,871.66፣
- ከአሥር ዓመት በላይ የቆየ ብር 8,223,232.04፣

2.3. <u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 34,643.49፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 8,000.00፣

2.4. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ ብር 3,161.40 የሚገኝ መሆኑ፤

2.5. <u>በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 3,948.35፣
- ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 170,171.42፣

2.6. <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከአንድ ወር አስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር 148,496.82፣
- ከአንድ ዓመት በላይ አስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር 381,077.27፣

በድምሩ ብር 26,834,173.78 ሳይከፈል ለረዥም ጊዜያት በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ከ2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም ጀምሮ የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ከአምስት እስከ ከአስር ዓመት እና ከአስር ዓመት በላይ ከቆየው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከተያዘው ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በ5004 የሂሳብ መደብ የተያዘው የደመወዝ የተጣራ ተከፋይ ብር 19,455,728.70 ለረጅም ዓመታት እየተንከባለለ የመጣ ቢሆንም ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ባለመወሰዱ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የሚታይ መሆኑ፤

3. በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት የተሰብሳቢና የተከፋይ ሒሳቦች የዴቢት ወይም የክሬዲት መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ከ2008 በጀት ዓመት ወደ 2009 በጀት ዓመት በተሰብሳቢና በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ለጀሮች ላይ የዞረው ከወጪ ቀሪ ሂሳብ መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ትክክለኛነት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ሲጣራ፡ -

3.1. <u>በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>

- ብር **20,335,184.59** ተሰብሳቢ ሂሳብ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፣
- ብር **239,721.61** ተከፋይ ሂሳብ ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፣

የታወቀ ሲሆን ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅት ሁኔታው ተጣርቶ አሰፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድ ባለበት ሁኔታ የሚገኝ መሆኑ፤

3.2. <u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ</u>

- ብር 5,038,380.71 ተሰብሳቢ ሂሳብ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፣
- ብር 2,216,491.67 ተከፋይ ሂሳብ ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፣

የታወቀ ሲሆን ስለሁኔታው በ2007 እና በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲጣራና ማስተካከያ እንዲሰራለት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ ሳይስተካከል በድጋሚ የተገኘ መሆኑ፤

3.3. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ብር 2,054.55 ተሰብሳቢ ሂሳብ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ ሲሆን፤ ብር 2,047.16 ተከፋይ ሂሳብ ደግሞ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑ፤

3.4. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ብር 293,367.62 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እና ብር 2,358,021.89 ተሰብሳቢ ሂሳብ ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ፤

4. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በግዥ መመሪያው እና በውሉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና የአመዘጋገብ ሥርዓቱም የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

4.1. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የመማሪያ ህንጻና የመሰብሰቢያ አዳራሽ ግንባታ ሥራን እንዲያከናውን ከቤዛ ኮንስትራክሽን የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር እንዲሁም የዶርሚቴሪና የምድረ ጊቢ ግንባታ ሥራን እንዲያከናውን ከ3 ኤም ኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ ለመሆናቸው ሲጣራ፡-

4.1.1. <u>ቤዛ ኮንስትራክሽን የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ</u>

- ብር 441,804.29 በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መኖሩ፣
- ብር 687,888.01 በብልጫ የተቀነሰ የቅድሚያ ግብር ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 3,617,462.64 ያልተመለሰ (ያልተቀነሰ) የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣

- ከላይ በተመለከቱት የሂሳብ ልዩነቶች ምክንያት ብር **2,487,770.34** በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ መኖሩ፣

4.1.2. <u>3ኤም ኢንጂነሪንግ እና ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር</u>

- ብር 171,062.14 በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መኖሩ፣
- ብር 609,963.04 በብልጫ የተቀነሰ የቅድሚያ ግብር መኖሩ፣
- ብር 1,220,812.98 ያልተመለሰ (ያልተቀነሰ) የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
- ከላይ በተመለከቱት የሂሳብ ልዩነቶች ምክንያት ብር 439,787.80 በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ መኖሩ፣

4.1.3. በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የሰራተኞች መኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራን ለማከናወን እንዲቻል ሳምሶን ገብረ ዮሐንስ ከተባለ የሕንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር እንዲሁም የተማሪዎች ማደሪያ ዶርሚተሪ ህንጻ ግንባታን ከሣይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትለው የተፈጸሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. <u>ሣይለም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር</u>

   - ብር 138,751.10 ያልተመለሰ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ መኖሩ፣
   - ብር 33,990.14 ያልተቀነሰ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ መኖሩ፣
   - ብር 31,180.31 ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
   - በተጠቀሱት ልዩነቶች ምክንያት ብር **203,921.55** በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ መኖሩ፣

2. <u>ሳምሶን ገብረ ዮሐንስ የሕንጻ ተቋራጭ</u>

   በውሉ ልዩ ሁኔታዎች (Special Conditions of Contract) ክፍል 8 ንኡስ ክፍል 1.1 መሰረት ጠቅላላ የግንባታ ስራው በ365 የካሌንደር ቀናት እንደሚጠናቀቅ ቢገልጽም የግንባታ ስራው መጠናቀቅ ከነበረበት ጊዜ ከ3 ዓመታት በላይ ከመዘግየቱም በተጨማሪም ተቋራጩ ሥራውን ሳያጠናቅቅ በ2008 በጀት ዓመት አቋርጦ የግንባታ መሳሪያዎቹን ከግንባታ ሥፍራው ያወጣ መሆኑ ተገልጾ ተገቢው

እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

4.1.4. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ

1. ኮሌጁ በገዋኔ ወረዳ በሙክቲዲላ (ኣሻካ) ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ውስጥ፡-
   - 1.1. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ፣
   - 1.2. የቆሻሻ ማስወገጃ ግንባታ፣
   - 1.3. የህንጻ ጥገና፣
   - 1.4. የውሃ መስመር ዝርጋታ፣
   - 1.5. የበግና የፍየል እርባታ ሰርቶ ማሳያ ግንባታ፣
   - 1.6. የእንስሳት ጤና ክልኒክ ግንባታ፣ እንዲሁም
   - 1.7. የዶሮ እርባታ ግንባታ፣

   እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል። ኮሌጁ ከተለያዩ የህንጻ ተቋራጮቹ ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

   - ብር 2,317,345.94 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 1,444,970.18 በብልጫ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለአሼቶ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የተፈጸመው ክፍያ ብር 71,530.00 በአማካሪው ከቀረበው የክፍያ ሰርተፊኬት በላይ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
   - ብር 2,835,538.85 ተመላሽ ተደርጎ ያልተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 31,263.20 ተመላሽ ያልተደረገ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 310,000.00 ከውል ውጭ በብድር ተሰጥቶ ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 224,457.86 በብልጫ የተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ መኖሩ፣
   - ብር 457,125.54 ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት መኖሩ፣
   - ብር 16,408.30 ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መኖሩ፣

- ብር 237,770.00 ተመላሽ ተደርጎ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 361,794.57 ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 22,055.84 በብልጫ የተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣
- ከላይ በተመለከቱት ልዩነቶች ምክንያት ብር 3,131,010.88 በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣
- ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሃ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሃ መስመር ዝርጋታው ፕሮጀክት የተጨማሪ ሥራዎች ውል ሳይኖር ብር የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ብር 408,459.30 ተጨማሪ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

የታወቀ ሲሆን በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ለልዩነቱ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሳይስተካከል ባለበት ሁኔታ እንደሚገኝ ለመገንዘብ የተቻለ መሆኑ፤

2. ኮሌጁ ከተለያዩ የግንባታ ተቋራጮች ጋር ውል ገብቶ የተለያዩ የግንባታ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሰረት የተጠናቀቁት የግንባታ ስራዎች ለታለመላቸው አላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

   2.1. ኮሌጁ ከአሊ ሞሚን ጠቅላላ የውሀ ነክ ስራዎች ተቋራጭ ጋር ለውሀ መስመር ዝርጋታ ግንባታ በብር 7,379,375.32 ውል የፈጸመና ሥራውም ተጠናቆ ከተቋራጩ ጋር ጊዜያዊ ርክክብ የፈጸመ ቢሆንም፡-

      - ☞ በውሃ መስመሩ ላይ ተዘርግተው የነበሩት በርካታ የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች ከመሀል የተነሱና በገዋኔ ከተማ በሚገኘው ውሀ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፣ በውሀ መስመሩ ላይ የቀሩት የውሀ ማስተላለፊያ ቧንቧዎችም ቢሆኑ አልፎ አልፎ የወላለቁ መሆኑ፣
      - ☞ ኮሌጁ የውሃ መስመሩን ዝርጋት ርክክቡ ከፈጸመበት ከመስከረም 30 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 60,000.00 የውሃ ማመላለሻ ቦቴ መኪና ተከራይቶ በጠቅላላው ብር 540,000.00 ለተጨማሪ

ወጪ የተጻረገ ከመሆኑም በላይ ወጪው አሁንም የቀጠለ መሆኑ፤

2.2. ኮሌጁ ከሁሴን ኢብራሂም ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ጋር በብር 9,221,913.25 የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል የፈጸመና ሥራው ተጠናቆ ርክክብ የተከናወነ ቢሆንም ለግንባታው የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ ማስወገጃ አብሮ ስላልተገነባለት ያለአገልግሎት ከሁለት ዓመታት በላይ ተቆልፎ የሚገኝ መሆኑ፤

2.3. ኮሌጁ ኤፍ ኤ ዋይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር ጋር በብር 5,468,710.00 የህንጻ ጥገና ግንባታ ውል የፈጸመ ሲሆን፣ ጥገናው ከመጋቢት 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስምንት ወራት ውስጥ ማለቅ እንዳለበት ቢጠቀስም ግንባታው ከመዘግየቱም በተጨማሪ የጥገናው ሥራ የተቋረጠ ቢሆንም ምንም ዓይነት ህጋዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

5. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማት የተከናወኑት የሒሳብ ማተካከያዎች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የተከተሉ መሆኑን እንዲሁም የሂሳብ ማስተካከያዎቹን አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡-

5.1. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለብር 82,954.55፣

5.2. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለብር **6,761,600.38**፣

በሂሣብ ምዝገባ ማዘዣ (ጆርናል ቫውቸር) ላይ በዴቢትና በክሬዲት የሂሳብ ማስተካከያ የተሰራ ቢሆንም ማስተካከያዎች ላይ ስህተቱ በየትኛው የወጪ ደረሰኞች ላይ እንደተፈፀሙ እና የሂሣብ ማስተካከያው እንዲሠራ ያስፈለገበት ምክንያት ያልተገለጸ በመሆኑ ምክንያት የማስተካከያ ሒሳቡን ትክክለኛነትና አግባብነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

6. ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 16(17) መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ተጠሪ ተቋማቱ ለፈጸሟቸው ግዥዎች ተገቢ ውል የፈጸሙ እና ክፍያዎችም በውሉ መሰረት የተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

6.1. <u>በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

6.1.1. ኮሌጁ ከኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር (Construction Design S.C.) ጋር በፈጸመው የማማከር አገልግሎት ውል መሰረት ብር 1,857,181.90 ክፍያ መፈጸም ሲገባው ኮሌጁ እስከ ሰኔ 30, 2010 ዓ.ም ድረስ ብር 4,025,000.00 ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል። ሆኖም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 16 (14) (5ለ) መሰረት የአማካሪው ስህተት ባልሆነ ምክንያት የውል ጊዜው በመራዘሙ የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ ከውሉ ጠቅላላ ዋጋ ከአስራ አምስት በመቶ (15%) የበለጠ መሆን እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም ኮሌጁ ለአማካሪው የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ብር ብር 2,167,818.10 ተጨማሪ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ተጨማሪ ክፍያው ከመጀመሪያው ውል ብር 1,857,181.90 ጋር ሲነጻጸር በ116.7% የጨመረ መሆኑ፣

6.1.2. በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(11) በአዋጁ አንቀጽ 51(1ሰ) እና 51(2) መሰረት ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ የውል ሥምምነት መፈረም እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም ኮሌጁ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ በተጨማሪነት ለፈጸመው ክፍያ ብር 2,167,818.10 የተጨማሪ የማማከር ሥራ ውል ሥምምነት ያልቀረበለት መሆኑ፤

6.2. የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለማማከር ሥራ የፈጸማቸው ክፍያዎች በውሉ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ከሳምሶን ገ/ዮሀንስ ጋር ተዋዉሎ የሚያሰራውን የሰራተኞች መኖሪያ ቤት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክስዮን ድርጅት የማማከሩን ስራ እንደሚሰራ የሚታወቅ ቢሆንም ኮንትራክተሩ የኮንስትራክሽን ስራዉን ሳይጨርስ አቋርጦ ከወጣ ከአመት ከስድስት ወር በላይ ሆኖት እያለ ድርጅቱ አገልግሎቱን ላልሰጠበት የማማከር ክፍያ በሚል ብር **115,469.70** ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

7. ከታህሳስ 1 ቀን 2008 ጀምሮ እንደገና ተሻሽሎ ባወጣዉ የዕቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ከብር 150,000.00 በላይ የሚፈጸሙ ሌሎች የአገልግሎት ግዥዎች በጨረታ መከናወን እንዳለባቸው ተመልክቷል። ሆኖም

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዳማ ከተማ በተለያዩ ቀናት በተለያዩ ሆቴሎች በጠቅላላው በብር **1,711,979.50** ለፈጸመው የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ ውስን ጨረታ ሳይወጣ በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤

8. ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ለተጠሪ ተቋማቱ ለ2009 በጀት ዓመት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ አለመደረጉ ሲጣራ:-

   8.1. በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከካፒታል በጀት ብር 187,482.13፣

   8.2. በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከካፒታል በጀት ብር 171,056.42 ፣

   8.3. በአርጻይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከካፒታል በጀት ብር **11,997.65**፣

   8.4. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከካፒታል በጀት ብር **108,363.79**፣

   8.5. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከካፒታል በጀት ብር **981,397.70**፣

በድምሩ ብር 1**,460,297.69** ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ መሆኑ፤

9. ሰኔ 2004 በወጣዉ የዉሎ አበል ክፍያ አፈፃጸም መመሪያ ክፍል 2 ተራ ቁጥር 4 ንዑስ ቁጥር 2 እና 3 መሰረት:-

   - የዉሎ አበል ተመኑ የተመሰረተዉ ከሙሉ አንድ ቀን የዉሎ አበል ተመን ዉስጥ 10% ቁርስ 25% ለምሳ 25% ለእራት እና 40% ለአልጋ በመመደብ፤
   - መሥሪያ ቤቱ የምግብ ወይም የመኝታ አገልገሎት የሰጠ እንደሆነ የተሰጠዉ አገልገሎት ሂሳብ ከላይ በተመለከተዉ ተመን መሰረት ከዉሎ አበል ተቀናሽ እንደሚሆን፤

ተመልክቷል። በመሆኑም፡-

   9.1. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓም ጀምሮ ባዘጋጀው ስልጠና ላይ የተከፈለ የውሎ አበል አግባብነት ሲጣራ፡-

9.1.1. ከየክልሉ የመጡት ሰዎች የደመወዝ መጠን የሚገልጽ ደብዳቤ እና ሰልጣኞቹ ከክልሉ ሲላኩ ከመጡበት ክልል አበል ያለመቀበላቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

9.1.2. ሰራተኞች በመንገድ ላይ ላሳለፉት ጊዜ የቀድሞው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ (የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር) ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ/30/ጠ13/40/883 ባወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ እና በወጡት የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ እንዲሁም ማወራረጃ ቅጾች መሰረት ቀርስ፣ ምሳና እራት በተጠቀሙበት ቦታ (ከተማ) እንዲሁም የአልጋ ክፍያ በጉዞ ወቅት ባደሩበት አካባቢ በወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት በዝርዝር ታስቦ መሞላትና መከፈል ሲገባው በመንገድ ላይ ቁርስ፣ ምሳና ዕራት የተጠቀሙበት ቦታ ባለመሞላቱ የክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

9.1.3. በሂሪቴጅ ፕላዛ ሆቴል በተደረገው የአራት ቀናት ስብሰባ ላይ በሆቴሉ ለአራት ቀን የምሳ አገልግሎት ቀርቦ ሳለ ለያንዳንዱ ሰራተኛ በድጋሚ ብር 13,443.00 የምሳ ዉሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣

9.1.4. ለውሎ አበል ተብሎ ከተፈጸመው የ15 ቀን ክፍያ ውስጥ ለአጠቃላይ ተሳታፊዎቹ ቢበዛ ለ2.35 ቀን ለመሄጃና ለመመለሻ፣ ለ4 ቀን በሂሪቴጅ ፕላዛ ሆቴል ለተደረገው ስብሰባ ቆይታ ለውሎ አበል ተብሎ የታሰበ ሲሆን፣ ለቀሪው ለ8.65 ቀናት የታሰበው የውሎ አበል ክፍያ ብር 116,281.95 በፕሮፖዛሉ ላይ እንደተመለከተው በተመረጡ ወረዳዎች፣ ቀበሌዎች በመገኘት የሞዴል ገበሬዎች ተሞክሮን በመመልከት የተግባር ላይ ሥልጠና እንደሚሰጥ የተገለጸ ቢሆንም የመስክ ላይ ሥልጠናው በየትኞቹ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ላይ እንደተደረገ በዝርዝር ያልተገለጸ በመሆኑ የክፍያውን አግባብነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

9.2. <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

9.2.1. የኮሌጁ ለሚገኙ ሰራተኞች በተሰማሩበት የስራ መስክ የተሻለ አፈጻጸም አቅም እንዲኖር በማቀድ ከየካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ለተከታታይ 15 ቀናት የክህሎት ስልጠና በሰጠበት ወቅት፡-

- ☞ ስልጠና ለሰጡ 17 መምህራን ከአራት ቀን አስከ ሰባት ቀን በጠቅላላው ብር 14,193.00 የዉሎ አበል ክፍያ ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ መሆኑ፣
- ☞ ለድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የምሳ አበል ብር 6,727.50 የተከፈለ መሆኑ፣
- ☞ ስለስልጠናው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ፕሮፖዛል ለኦዲት እንዲቀርብ ቢጠየቅም ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣

9.2.2. የኮሌጁ ሰራተኞች የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ሲሄዱ ክፍያው በአሶሳ የአበል መጠን ብር 171 መሰረት ተሰልቶ መከፈል ሲገባው ብር 200 በመከፈሉ:-

- ☞ ለ65 ሰራተኞች በጠቅላላው ብር 11,960.00 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ☞ የመንግሥት ተሿሚ ሳይሆኑ ለኮሌጁ ምክትል ዲን ለስምንት ቀን ብር 1,416.00 መከፈል ሲገባው በቀን 500 ሂሳብ በጠቅላላው ብር 4,000.00 በመከፈሉ ምክንያት በብልጫ ብር 2,584.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
- ☞ ለሶስት የኦዲዮ ቪዥዋል ሰራተኞችና ለጋዜጠኞች የስምንት ቀን የውሎ አበል በቀን ብር 200 በጠቅላላው ብር 1,600.00 ተከፍሏቸው እያለ በድጋሚ ለ7 ቀን ለአንድ ሰው በቀን ብር 200.00 ለአራት ሰው በጠቅላላው ብር 4,200.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

በአጠቃላይ የሚዛን ኮሌጅ ከውሎ አበል መመሪያ ውጪ ብር 39,664.50 የውሎ አበል ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

10. በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 34/2 መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የትርፍ ሰዓት ሥራ አከፋፈል መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 በተጻፈ ደብዳቤ የቀድሞው የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ያሳወቀ ቢሆንም ኤጀንሲው እንደገና ጳጉሜ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/13/37/820 በተጻፈ ደብዳቤ የትርፍ ሰዓት ክፍያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ ማሳወቁ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለኦዲት ሥራ በናሙና ከተመረጡት ወጪዎች ውስጥ መሥሪያ ቤቱ

የፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴርን ሳያስፈቅድ ብር 172,198.09 የትርፍ ሰዓት ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

11. ከ1998 ዓ.ም በፊት ጀምሮ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ለየኮሌጆቹ ለሥራ ማስኬጃ የላከው ሂሳብ በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ በ2009 በጀት ዓመት እንዲወራረድ የተደረገ ሲሆን፣ ለተወራረደው ሂሳብ በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሠረት የተሟላ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

  11.1. በጋምቤላ ኮሌጅ በ1998 በጀት ዓመት ለተግባር ትምህርት ለወጡ ተማሪዎች ለሁለት ወር ቀለብ በጠቅላላው ብር 8,160.00 በክልሉ ግብርና ገጠር ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ ገንዘብ ያዥ በሆኑ በአቶ ኡቻን ኢቦንግ በኩል ለተማሪዎቹ የተከፈለ መሆኑ ተገልጾ ሂሳቡ ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 176300 እንዲወራረድ የተደረገ ቢሆንም ተማሪዎቹ ገንዘቡን ስለመቀበላቸው የሚያሳይ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡ እንዲወራረድ መደረጉ፤

  11.2. በ2004 እና የ2005 በጀት ዓመት ከአላጌና ከአርዳይታ ግ/ቴ/ሙ/ኮሌጅ ለተግባር ልምምድ ወደ ጋምቤላ ግ/ቴ/ሙ/ኮሌጅ ለሄዱ ተማሪዎች ለቤት ኪራይ ወጪ ብር 284,635.00 በተሰብሳቢ ተይዞ የነበረ ሲሆን ሂሳቡ ሰኔ 22 ቀን 2009 ዓ.ም በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 176296 እንዲወራረድ ሲደረግ ማስረጃ የቀረበው ሰነድ ከተወራረደው ሂሳብ ጋር ሲነጻጸር በብር 50,750.00 ያነሰ መሆኑ፤

  11.3. ለተለያዩ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎች ለተፈጸሙ ክፍያዎች ብር 88,178.33 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

በድምሩ ለብር 147,088.33 የወጪ (የክፍያ) ማስረጃ አለመቅረቡ፤

12. በገቢ አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 12 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል ቦነስ የአመት ፍቃድ ክፍያ የአገልግሎት ካሳ … ወዘተ) ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1 አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን አሳዉቋል።

ይሁን እንጂ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሚያዝያ 18 ቀን 2009 በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/33/202 ከኃላፊነት የተነሱ የሀገርና የመንግሥት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኙዋቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 653/2001 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1003/2009 እንዲሁም አዋጁን ተከትሎ በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በገንዘብ ተሰልተው ለባለመብቶቹ በአንድ ጊዜ የሚሰጡ ጥቅሞችን የጡረታ መዋጮ ማካካሻ መጠንን በሚመለከት ሂሳቡ ተሰልቶ ለሚመለከታቸው እንደሚያስተላልፍ ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት ለቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ዴኤታ፣

- የመቋቋሚያ አበል ብር 128,601.00፣
- የመኖሪያ ቤት አበል ብር 120,000.00፣
- የተሽከርካሪ አበል ብር 22,572.00፣

በጠቅላላ ብር 271,173.00 የጥቅማ ጥቅሞች ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ከክፍያው ላይ ብር 93,410.55 የሥራ ግብር መቀነስ ሲገባው ለቤት አበል የተፈጸመው ክፍያ ሳይካተት የሥራ ግብር በመቀነሱ ምክንያት ብር 49,910.55 ብቻ በመቀነሱ ብር 43,500.00 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤

13. በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ንብረቶች ተገዝተው በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሠረት በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ገቢ የሚደረጉ መሆኑን በናሙና ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በጋምቤላ እና አሶሳ ክልል ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ ሂሳብ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ለስራ ማስኬጃ ተልኮ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሳብ በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ እንዲወራረድ ከተደረገው ሂሳብ ውስጥ የ2009 በጀት ዓመት አካል ሆነው በወጪ ለተመዘገቡት በብር 37,506.00 ለተገዙት ንብረቶች የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

14. የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን በተሟላና በተገቢው ሁኔታ የሚመዘግብ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለቅድሚያ ክፍያ የተሰጠው ሂሳብ ብር 29,000.00 በዴቢት 4211 እና በክሬዲት 4103 ተብሎ የተመዘገበ ሲሆን፣ ለቅድሚያ ክፍያ ከተሰጠው ሂሳብ ውስጥ ብር 24,700.00 ሲወራረድ በዴቢት 6258 እና በክሬዲት በ4211 ተብሎ መወራረድ ሲገባው በክሬዲት 4103 የሂሳብ መደብ ተብሎ ተወራርዶና ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤

15. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ተጠሪ ተቋማቱ አዲስ ለሚቀጥሯቸው ሠራተኞች የከፈሉት ደመወዝ ሰራተኞቹ ከተቀጠሩበት ቀን ጀምሮ መሆኑንና ለለቀቁት ሠራተኞች ደግሞ ላልሰሩበት ጊዜ ክፍያ አለመፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

15.1. በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ሶስት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ በጠቅላላው ብር 4,728.72፣

15.2. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ሁለት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ በጠቅላላው ብር 9,250.33፣

15.3. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ አንድ ሰራተኛ ከስራ ከለቀቁ በኋላ ብር 5,615.00፣

በድምሩ ብር 19,594.05 ከስራ ከለቀቁ በኋላ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

16. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለፈጸማቸው ክፍያዎች በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ተራ ቁጥር 6 መሰረት የተፈቀደ በጀት ለመኖሩ፣ የተሟላ ማስረጃ የቀረበላቸው ለመሆኑ እና የክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም የኮሌጁ የስፖርትና መዝናኛ ክበቡ ለኮሌጁ በጻፈው ደብዳቤ በኮሌጁና በአካባቢው ወረዳው ከባለፈው አጋማሽ አመት ጀምሮ ተከስቶ በነበረው የፀጥታ ችግር የኮሌጁንና የአከባቢውን ፀጥታ ለማስከበር የመጡ የመከላከያ አባላት፣ የኦሮሚያ ፖሊስ ሠራዊት አባላትና የወረዳችን ፖሊሶች ጭምር ወደ ኮሌጁ ሲመጡ ከካፍቴሪያው የመስተንግዶ አገልግሎት ሲያገኙ የቆዩ መሆኑን ጠቅሶ በወቅቱ ከፍተኛ የዋጋ ውጣ ውረድ የነበረ በመሆኑና አንዳንድ ጊዜ ሰራዊቱ ከግዳጅ መልስ በእኩለ ለሊት ጭምር የምግብና የትኩስ መጠጥ መስተንግዶ ይሰጥ ስለነበረ ካፍቴሪያው ሳይመዘግባቸው የቀሩ አገልግሎቶች ስላሉ ኮሌጁ ካፍቴሪያውን እንዲደጎም በጠየቀው መሰረት ኮሌጁ ከውስጥ ገቢ ብር 15,000.00 ለካፍቴሪያው የድጎማ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

17. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 30 ተራ ቁጥር 2(ሀ) መሰረት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግብር ነጻ መሆናቸው ተደንግጓል። ሆኖም የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ከመሆኑም በተጨማሪ ለትርፍ ያልተቋቋመ በመሆኑ የንግድ ትርፍ ግብር የማይመለከተው ሆኖ

ሳለ ኮሌጁ ከደቡብ ምርጥ ዘር ድርጅት ጋር ምርጥ ዘርን ለማባዛት በገባው ውል ስምምነት መሠረት ኮሌጁ ካገኘው ገቢ ብር 609,226.87 ውስጥ ድርጅቱ 2% የቅድሚያ ግብር ብር 12,184.53 ቀንሶ ያስቀረ መሆኑ፤

18. የካቲት 8/2002 አ/ም በቁጥር ታክ/ቀ/5/102 በገቢዎ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ባወጣዉ መመሪያ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸዉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 5,000.00 በላይ ከሚፈጸሙት ግዢ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያዉን በመቀነስ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸዉ፤ በተጨማሪም ከዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች ላይ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 መሰረት የቅድሚያ ግብር (2%) መቀነስ እንዳለበት ተመልክቷል። ይሁን እንጂ በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ኮሌጁ የተለያዩ የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ከታክሱ ተመዝጋቢዎች ላይ ሲፈጸም፡-

18.1. ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 946320 ለተማሪዎች ቀለብ (ነጭና ቀይ ሽንኩርትና ድንች) ከመልካሙ በለጠ አትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ግዥ ሲፈጸም የተቀነሰው የቅድሚያ ግብር ብር 362.07፣

18.2. ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 946303 የተማሪዎች ቀለብ (ጤፍ፣ ሩዝ፣ አተር፣ ምስር ክክና እርድ) ከይማም መሀመድ እህል አቅራቢ ግዥ ሲፈጽም የተቀነሰው ብር 6,640.86 የቅድሚያ ግብር፣

በጠቅላላው ለተቀነሰው ብር 7,002.93 የቅድሚያ ግብር ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤

ታውቋል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 18 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

1. <u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች</u> <u>(Emphasis of Matters)</u>

1.1. በፋይናንስ መመሪያው መሠረት በግዥና በዕርዳታ ለሚገቡ ዕቃዎች የሚከፈለው የቀረጥ ሂሳብ ለሂሳብ አሰራር እንዲያመች ጥሬ ገንዘብ ነክ ባልሆነ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን በናሙና ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጻፈለት ደብዳቤ መሠረት በግዥና በዕርዳታ የገቡ የላቦራቶሪ መገልገያ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ አከናውኗል። ሆኖም ዕቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው ከወጪ ሂሳቡ ጋር የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ ባለመደረጉ ብር **105,770,570.73** ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

1.2. ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ለተጠሪ ተቋማቱ በ2009 በጀት ዓመት ለመደበኛና ለካፒታል ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለው ሲታይ፡ -

1.2.1. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከመደበኛ በጀት ብር 28,839,667.52፣

1.2.2. በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ከካፒታል በጀት ብር 2,344,143.04፣

1.2.3. <u>በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከካፒታል በጀት ብር 4,563,160.94፣
- ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 11,429,727.50፣

1.2.4. <u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከካፒታል በጀት ብር **675,639.17**፣
- ከውስጥ ገቢ በጀት ብር **874,173.56**፣

1.2.5. <u>በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከካፒታል በጀት ብር 4,659,470.25፣
- ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 6,031,771.77፣

1.2.6. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ከካፒታል በጀት ብር **6,371,045.11**፣

1.2.7. <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ከካፒታል በጀት ብር 2,430,466.01፣
- ከውስጥ ገቢ በጀት ብር 314,915.60፣

በድምሩ ከብር 68,534,180.47 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፤

1.3. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የካቲት 2002 በገኸው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም ባወጣው መመሪያ ቁጥር 27/2002 ክፍል 6 ተራ ቁጥር 4 ወኪሉ በወሩ ውስጥ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ የያዘውን ታክስ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ገቢ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ ከነሀሴ 2008 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም ድረስ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ ቀንሶ የያዘውን ብር 702,666.20 በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለግብር ሰብሳቢው በለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ቀን 2009 ገቢ ያደረገ መሆኑ፤

1.4. በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 አንቀጽ 53/3 መሠረት ከተከፋይ ሂሳብ ግብሩን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ያለበት መሥሪያ ቤት በወሩ ውስጥ ከተከፈሉ ሂሳቦች ላይ ቀንሶ ቀሪ ማድረግ የሚገባውን አጠቃላይ ሂሳብ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም ኮሌጁ ከነሀሴ 2008 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2009 ዓ.ም ድረስ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ ቀንሶ የያዘውን ብር 255,165.87 በመመሪያው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ለግብር ሰብሳቢው በለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ገቢ የተደረገ መሆኑ፤

1.5. የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት በ2009 በጀት ዓመት ለፈጸመው ክፍያ በጀት የያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ በማስተባበሪያው ሥር ላሉ ኮሌጆች ለመማር ማስተማር ሂደት የሚያገለግሉ ዕቃዎችን የህዝባዊ ሪፑብሊክ ቻይና መንግሥት በእርዳታ የለገሰ ሲሆን፣ ንብረቶቹ በጅቡቲ ወደብ ከደረሱ በኋላ እ.ኤ.አ ጁን 26 ቀን 2016 ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤቱ ለመጋዘንና ለወደብ ኪራይ ከፈጸመው ክፍያ ብር 484,581.59 ውስጥ እ.ኤ.አ ከጁላይ 18 ቀን 2016 እስከ እ.ኤ.አ ፌብርዋሪ 28

ቀን 2017 ድረስ ንብረቶቹ ለስምንት ወራት ያህል ከወደቡ ባለመነሳታቸው ምክንያት ለመጋዘንና ለወደብ ኪራይ ተጨማሪ ክፍያ ብር 336,416.43 የፈጸመ መሆኑ፤

1.6. የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሀሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 ማናቸውም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ በወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ መረጋገጥ እንዳለበት በተመለከተው መሰረት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ አሰራሩ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ:-

1.6.1. በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ብር 212,313.98 ለተለያዩ ግዥዎች ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤

1.6.2. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ብር 1,870,124.83 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤

1.6.3. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ብር 1,693,822.08 በወጪ ማስመስከሪያ ደረሰኞች ላይ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ እንዲሁም ስለሂሳቡ ትክክለኛነት በፊርማ ያልተረጋገጠ መሆኑ፤

1.7. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ የገቢ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1.7.1 የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ ከሲኦሲ (COC) ምዘና የሰበሰበውን ገቢ በ1443 መመዝገብ ሲገባው ብር 21,000.00 በሂሳብ መደብ 1489 የመዘገበ መሆኑ፤

1.7.2 የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በጀት ዓመቱ ከግብርና ምርት ሽያጭ የሰበሰበውን ገቢ በሂሳብ መደብ 1455 እንዲሁም ከማታ ትምህርት የሰበሰበውን ገቢ ብር 882,656.62 በ1443 መመዝገብ

ሲገባው በሂሳብ መደብ 1489 መመዝገቡ የታወቀ ሲሆን፣ ስለሁኔታው በ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በአሁኑ ኦዲትም ሳይስተካከል በድጋሚ የተገኘ መሆኑ፤

1.8. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ የወጪ ሂሳቦች የሚመዘግቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ:-

1.8.1. በኢጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለተለያዩ ክፍያዎች የተፈጸመው ብር 16,400.00 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

1.8.2. በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለተለያዩ ክፍያዎች የተፈጸመው ብር 463,230.47 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

1.8.3. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለተለያዩ ክፍያዎች የተፈጸመው ብር 182,915.31 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

1.9. ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 3 አንቀፅ 8 ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግሥት መ/ቤትና በስሩ የተደራጁ አካላት የታቀዱ የስራ ፕሮግራሞቻቸዉን ተግባራዊ ለማስደረግ የሚያስፈልጋቸዉን ግዥ በወቅቱ ለመፈጸም የሚያስችል በመርሃ ግብር የተደገፈ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እንደሚገባና ዕቅዱም ለግዢ ኤጀንሲ መላክ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም የገዋኔና የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች በ2009 በጀት ዓመት የግዥ እቅድ ያላዘጋጁ እና ለግዢ ኤጀንሲ ያላኩ መሆኑ፤

ታውቋል።

2. ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

2.1. የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና የተጠሪ ተቋማቱ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 እና በመንግሥት ቋሚ ንብረት አስተዳደር ማንዋል (ጎፋም) መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

2.1.1. <u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ</u>

1. በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሠረት የስቶክ መዛግብቶችን የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሠራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው የተመለከተ ቢሆንም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሁሉም የንብረት ዕቃ ግምጃ ቤቶች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀትና የመመዝገብ፣ ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነቶች ሥራ በንብረት ግምጃ ቤቶቹ ሰራተኞች የሚከናወን መሆኑ፤

2. በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) በመሥሪያ ቤቱ ኮምፒተራይዝድ በሆነ መልኩ የተዘጋጀ እና አገልግሎት አየሰጠ መሆኑ ቢታወቅም እያንዳንዱ ሰራተኛ ንብረት ሲውስድ አልፎ አልፎ ተፈርሞ በሀርድ ኮፒ የማይቀመጥ መሆኑን በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ጋር ንብረት ተከፋፍሎ መሥሪያ ቤቶቹ የተለያዩ ቢሆንም አልፎ አልፎ ወደ እንስሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር የሄዱት ሰራተኞች በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ኮምፒተራይዝድ በሆነው ፋይል ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤

3. በካዛንችስ አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት የታይፕ ወረቀቶች ብዛት 76፣ የታይፕ ሪቫን ብዛት 7፣ ፊሊፕ ቻርት ብዛት 100፣ Epson የፕሪንተር ሪቫን 7754 ብዛት 104፣ IBM Ribbon ብዛት 12፣ Cannon Cartridge Film Ribbon ብዛት 19፣ ፎቶ ኮፒ ቶነር 2030 ብዛት 3፣ የፓርከር መቀያየሪያ ብዛት 27፣ የቲተር ቀለሞች እና ሌሎችም አገልግሎት የማይሰጡ የጽህፈት ዕቃዎች ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ ከመሆኑ በተጨማሪም አገልግሎት መስጠት የሚችለው ንብረት አገልግሎት ከማይሰጠው ጋር ያልተለየ መሆኑ፤

4. <u>በሳሪስ ማዕከላዊ የመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- አብዛኛዎቹ ዕቃዎች ቢን ካርድ የተዘጋጀላቸው ቢሆንም ካርዱ ዕቃዎች ላይ በተሟላ መልኩ እንዲንጠለጠል ያልተደረገ መሆኑ፤

- የተለያዩ አገልግሎት የማይሰጡ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

5. <u>በሳሪስ ቁጥር ሁለት ማዕከላዊ የከባድና ቀላል ዕቃዎች ግምጃ ቤት፤</u>

   - የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ የህንጻ መሳሪያዎች፣ የቧንቧ ዕቃዎች፣ ዶማ፣ የዓሳ መያዣ ክር እና 14 ተሸከርካሪ ወንበሮች አስሩ ሳይገጣጠሙ እና ፍሪጆች ለረጅም ዓመታት ያለስራ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
   - በኮንቴነሮቹ ውስጥ የሚገኙ እና ኮንቴነሮቹ ቢከፈቱ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች፣ የደረቁ ማዳበሪያዎች፣ የጓሮ አትክልት ዘር፣ ኮንዲዩት (ለሕንጻ ሥራ የሚያገለግል)፣ የምግብ ዘይት፣ የቅባት እህሎች በኮንቴሮቹ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
   - በግቢው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ብዛት ያላቸው አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ጎማዎች፣ ብረታ ብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤

6. በዕጽዋትና የአዝርዕት ኬሚካሎች ዕቃ ግምጃ ቤት ግቢ ውስጥ ከቆርቆሮ የተሰሩ በርሜሎች ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኙና በተለያዩ መጋዘን ውስጥ ተመላሽ የተደረጉ የተለያዩ ፍራሾች፣ ጀሪካኖችና የውሃ መቅጃ ባልዲዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

7. በሳሪስ ዕቃዎች ግምጃ ቤት አሮጌ ፕላስቲክ የፈልድ ድንኳኖች፣ የድንኳን ጠረጴዛና ወንበሮች፣ መዶሻዎች፣ ኬሚካል መርጫ መሳሪያ፣ ኦክሲጂን 4 እና የላብራቶሪ ዕቃዎች (ለምሳሌ ከ1991 ዓ.ም ጅምሮ የሚገኝ Rate tender ብዛት 715፣ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኝ Filter Paper ብዛት 32 Pack፣ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኝ Xylene Bottle ብዛት 78፣ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኝ Pyrex Flu ብዛት 432 ፣Round Filter ብዛት 40፣ Killing Jar Large ብዛት 15 Condit 18 mm ብዛት 750 22mm ብዛት 650 pipe pvc 100mm ብዛት 14 live animal cage trap for rat ብዛት 386) ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

8. በቃሊቲ በተለያዩ ግምጃ ቤቶች ለጤና እና ለአካባቢው አስጊ የሆኑ የሚወገዱ ኬሚካሎች፣ ከ20 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጠ ከሰላሳ ሺ በላይ የሚሆን ለጸረ ተባይ መርጫ የሚሆን የባትሪ ድንጋይ፣ ባለ 25 ሊትር በርሚሎች፣ አገልግሎት መስጠት የሚችል የጓሮ አትክልት ኬሚካል መርጫ (kioritz Battery powered spray) ብዛት 1,150፣ የተሰባበሩ የቢሮ ዕቃዎች፣ ወንበር፣ ሼልፍ፣ ጠረጴዛ፣ የባኞና የሽንት ቤት ዕቃዎች፣ ፍሪጅ፣ የአይዋ ወጥመድ፣ የፈረስ ኮርቻ የለስላሳ ጠርሙሶች፣ ከቀርከሃ የተሰሩ ትንንሽ ሙቀጫዎች፣ እጅግ በጣም ብዙ የኮምፒዩተር ሞኒተር፣ አዲስ አገልግሎት ያልሰጠ ፕሮጀክተር ብዛቱ 42፣ ቴሌቭዥኖች፣ የኦዲዮ ቪዡዋል እቃዎች፣ የተሰባበሩ የጋራጅ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

9. በቃሊቲ የተመላሽ ዕቃዎች ግምጃ ቤት በርካታ የመንገድ አልጋዎች፣ ፍራሾችና ትራሶች፣ የተለያዩ የላብራቶሪ ማሽኖች፣ መጋረጃዎች፣ ድንኳኖች ከነካስማው፣ የቡና ጥራት መቅመሻ ዕቃ፣ ፋይሊንግ ካቢኔት፣ ስሊፒንግ ባግ፣ ፍሪጆች እና 10 የካርታ ማተሚያ፣ በተለያዩ መጋዘኖች የሚገኙና በግቢው ውስጥ ሜዳ ላይ እና ጥግ ጥጉን ወድቀው የሚታዩ የጨፍ መዝሪያ ባለ 2 ሌቨል (Level) ብዛት 204 እና ባለ 3 ሌቨል (Level) ብዛት 329፣ 4 ፍሪጆች፣ 4 የእሳት ማጥፊያ ፣ የውሃ ማሞቂያ 2 እና በተጨማሪም በርካታ በነዳጅ የሚሰሩ ማረሻና ማለስለሻ ያለምንም አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

ሲሆን በአብዛኛዎቹ ላይ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ እንዲወሰድ አለመደረጉ፤

2.1.2. <u>በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. በኮሌጁ ለሚማሩ ተማሪዎች ምግብ ለማዘጋጀት የሚውሉ ግብአቶች ለታለመለት አላማ የሚውሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ለተማሪዎች የምግብ እቃ ግምጃ ቤት ሚኒ እስቶር (Mini Store) እና ወፍጮ ቤት ገቢ ከሆኑት ውስጥ በጠቅላላው

ዋጋቸው ከብር 203,495.00 በላይ የሆኑ ሽቀጣ ሽቀጥና ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በሞዴል 22 ወጪ ተደርገው በራሱ ገቢ ለሚንቀሳቀሰው ለኮሌጁ የሰራተኞች መዝናኛ ክበብ (Cafeteria) በብድር የተሰጡ ቢሆንም ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ፤

2. ኮሌጁ ብር 184,923.00 የሚያወጡ ለሽያጭ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ እንስሳቶችንና የእንስሳት ውጤቶችን ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ለኮሌጁ የሰራተኞች ክበብ (ካፍቴርያ) በዱቤ የሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

3. <u>በኮንስትራክሽን ዕቃዎች ግምጃ ቤት</u>፤

- ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- 58 ፓኬት 3/12 የሆነ ቪቴ፣ 3 የጋሪ እግር፣ 45 ባለ 3 ጣት መኮትኮቻ፣ 15 በመጠን የሚለያዩ አልቪሎች (የብረት መቀጥቀጫ)፣ 400 ሜትር የኢንተር ኮም እና 300 ሜትር የማይክ ኬብል ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 941 ፍሬ ሲንግል ብራኬት የእንጨት ማስነከሻ ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 45 ፓኬት ረጅም የአልጋ ጋንች ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 68 እስኳድራ ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው መገኘታቸው፤
- 11 ሴራሚክ የሶፍት መስቀያ፣ 2 የሽንት ቤት እና 2 የሻወር ሲንክ፣ 7194 የተለያየ መጠን ያላቸው እርበር ካፕ፣ 6 ያገለገሉ ጉጠት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ከ400 በላይ የሚሆን አጭር የአልጋ ጋንች፣ 33 ፓኬት ባለ10 እስክሮ፣ ከ 2480 በላይ የሚሆኑ ትንሿ የሳጥን ማጠፊያ፣ 73 ፓኬት አንድ ሙሉ ¼ በሰባት የሆነ ቪቴ ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ

ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- 7 የብረት ሞርሳ፣ 10 በሁለት ሰው እና 10 በአንድ ሰው የሚያዝ የእንጨት መቁረጫ መጋዝ፣ 60 የእንጨት ማህሌት (መዶሻ)፣ 3 ሽብልቅ (ድንጋይ መፍለጫ) ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 2ጂ- ክለምን፣ 5 ዌልዲንግ ክላፕ፣ ከ45 በላይ የሚሆኑ የተለያ መጠን ያላቸው መፍቻዎች፣ 22 አካፋ፣ 71 የወርክ ሾፕ መጋዝ፣ 176 ሞለድ እና 324 መጋዝ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 17 የቁም ማጭድ፣ 3 Hand Dril፣ 16 የተሽከርካሪ ወንበር እግር፣ 48 ባለ 3ጣት ዶማ፣ 60 ባለ 125 እና 24 ባለ 160 ካስትል ጎማ፣ 116 ሁክ (መቆፈሪያ)፣ 193 ያገለገሉ ባለ አንድ ጣት ዶማ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 10 Genber Corerers ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 76 የበር ማጠፊያ (Hinges 3 Hole) ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 269 ሬክ መቧጠጫ እና 394 ገሶ (መሬት መቆፈሪያ) ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- የተለያዩ ሰነዶች ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- የተበላሹ ሁለት ባለ8 ችቡድ በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- 5 ወጪ የሆኑ ላሚራዎች ከ 4ወር በላይ በግምጃ ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

4. በተማሪዎች ምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤

5. በነዳጅ፣ ዘይትና ቅባት ግምጃ ቤት በርካታ በገበሬዎች ሁለገብ ማሰልጠኛ ጽሕፈት ቤት ስም የታተሙ ደረሰኞች፣ የምስክር ወረቀቶችና የተለያዩ ሰነዶች ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

6. <u>በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- አምስት 1000ML፣ ስድስት 50ML፣ አራት 100ML፣ ሶስት 500ML በድምሩ 18 ቤከሪ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 9 Valumatics 250ML፣ 84 Valum tube 1ML፣ 1 Pestle & Morese፣ 30 Pepates of 5ML፣ 1 Flascs of 500ML፣ 4 Grind Silinder 250ML፣ 1 White Stem 100ML፣ 1 Beanch Vise፣ 1 Major Jar 2000cc፣ 2 Gest Sprice፣ 3 Grand Celender 500cc & 4 Grand Celender 400cc፣ 8 Explonation Compas እና 2 Reac stro Machine ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 2 ቴምራ የስህል ቀለም እና 6 የዘይት ቀለም ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 7 ኢንች ጄት 45 ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 7 የፎቶ ኮፒ ቶነር ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 3 ዚፕ ዲስክ፣ 1 ሚዲየም ኢንተርቫል ላይት፣ 2 PC Toner NP 1010፣ 3 Scren Fieter 17 ench፣ 10 Screne Projection for tab፣ 50 Film Phoma፣ 3 Spayeral wepe፣ 6 Mirror Sterco Scop፣ 18 Rapido

Graph tech pens፣ 5 Plastic Scraper እና 7 Soil Thermo meter ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- ከሁለት መደርደሪያ በላይ የላብራቶር ዕቃዎች ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- 3T- Square ማስመሪያ ካልታወቀ ጊዜ ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- የአንዱ ዋጋ ብር 70 የሆነ 160 ቲሸርት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

7. የተሽከርካሪ መለዋወጫ ተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤

8. <u>የእንስሳት መድሃኒት ግምጃ ቤት</u>፤

- ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- በርክክብ ቅጹ ላይ ርክክቡ የተደረገበት ቀን ያልተጻፈ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈበት መድሃኒቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

9. <u>የእንስሳት መድሃኒት ሚኒ እስቶር</u>፤

- ቢን ካርድ ከዕቃው ጋር አብሮ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈበት መድኃኒቶች ተቀምጠው መገኘታቸው፤
- በርካታ ያገለገሉ ዕቃዎች ከሁለት ዓመት በላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደ መሆኑ፤

10. በእንስሳት መኖ በማቀነባበሪያ ቤቱ ውስጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈባቸው (የተበላሹ) መኖ(ፍሩሽካ) ካልተበላሹ መኖዎች ጋር አንድ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

11. <u>የጥጆች በረትን በተመለከተ፤</u>

- በበረቱ በር ላይ የሚገኘው የእግር መንከሪያ ኬሚካል (Phoot Path) የተበላሸ መሆኑ፤
- በበረቱ የሚገኘው የጥጆቹ መመገቢያ ባልዲ ከመበላሸቱ የተነሳ ለጥጆቹ አመቺ አለመሆኑ፤
- የጥጆቹ መውጫና መግቢያ በር የተገነጠለና በእንጨት ተደግፎ የቆመ መሆኑ፤
- በረቱ ጽዳቱ ያልተጠበቀ መሆኑ፤

12. <u>የወተት ማቀነባበሪያን በተመለከተ</u>

- 1 ትልቅ ዲፕ ፍሪጅ፣ 2 ረጃጅም ፍሪጆች እና 1 ዲፕ ፍሪጁን የሚያንቀሳቅስ የኤሌክትሪክ ማሽን ለበርካታ ዓመታት ያለምንም አገልግሎት በማቀነባበሪያው ውስጥ ተቀምጠው መገኘታቸው፤
- የማቀነባበሪያው ክፍል የውሃ ፍሳሽ መስመር የተበላሸ መሆኑ፤

13. የተማሪዎች ጤና ጣቢያ መድሃኒት ግምጃ ቤት ውስጥ 57 First Aid Kit፣ 5 Delivery Kit፣ 9 Phyesitian Kit፣ 2 Shever፣ 4 Cellona (6*3%)፤ 6 Cellona (10*275) ፣ 3 ሲሊንደር፣ 4 የድሮ ሞዴል ማይክሮስኮፕ ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ ያለምንም አገልግሎት በግምጃ ቤቱ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

14. የተማሪዎች ጤና ጣቢያ መድሃኒት ሚኒ እስቶር በግምጃ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜያቸው ያለፈበት መድሃኒቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

2.1.3. <u>በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. ኮሌጁ ለሚገዛቸው እህሎች ተገቢውን ውል መግባቱንና በውሉ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ኮሌጁ ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውል ጤፍ ከየሱፍ ሂርጶ ለመግዛት መስከረም 29/2008 ውል የተዋዋለ ሲሆን በውሉ ተራ ቁጥር 6 አቅራቢው የምግብ ጥሬ እቃዎቹን በውድድር ወቅት

ባቀረበው ናሙና መሰረት በሚፈለገው ጥራት 1ኛ ደረጃ ለግዢ ፈጻሚው ለማቅረብ ግዴታ ገብቷል። ከዚህም በተጨማሪ በውሉ ተራ ቁጥር 11 ደግሞ አቅራቢው የገባውን ግዴታ ባለመወጣቱ የምግብ ጥሬ እቃዎቹን በገባው ውል በሚፈለገው ጥራት ባቀረበው ናሙና መሰረት ባለማቅረቡ በግዢ ፈጻሚው ላይ ጉዳት ካደረሰበት የተያዘው የዋስትና ገንዘብ ማለትም ብር 512,400.00 ለግዢ ፈጻሚው ገቢ እንደሚደርግ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተዋል። ነገር ግን የሱፍ ሂርጳ በ2008 ዓ.ም. በተለያዩ ጊዜያት ካቀረባቸው 1,565.69 ኩንታል ጤፍ ውስጥ 325 ኩንታል የሚሆን የተበላሸ ወይም ከአሸዋ ጋር የተቀላቀለ ጤፍ ቢሆንም ኮሌጁ ጤፉን ለአቅራቢው በጊዜው መመለስ አሊያም በፍርድ ቤት ከሶ አቅራቢው ለዋስትና ካስያዘው ብር 512,400.00 ውስጥ እንዲከፈለው መጠየቅ ሲገባው ኮሌጁ ብር 416,325.00 በውሉ መሰረት ላልቀረበለት ጤፍ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን በዚሁ ምክንያት 325 ኩንታል ጤፍ ያለአገልግሎት በኮሌጁ ወፍጮ ቤት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑ፤

2. <u>በጋራዥ የሚገኝ የመኪና ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ አዳዲስ ጎማዎች አገልግሎት ከማይሰጡ የመኪና ተመላሽ መለዋወጫዎች ጋር ተከማችተው ከመቀመጣቸው በተጨማሪ እስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ 17 የሞተር ሳይክሎች፣ 215 የመኪና እና የትራክተር ጎማዎች፣ ከ20 በላይ የሞተር ሳይክል ጎማዎች፣ ጄኔሬተር፣ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ 1 ቤለር፣ 2 ዶዘሮችና 1 ኮምባይነር ያለ አገልግሎት ከአንድ ዓመት በላይ ፀሃይና ዝናብ እየተፈራረቀበት የሚገኝ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለ መሆኑ፤

3. <u>የመድኃኒት ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- በግምጃ ቤቱ ውሰጥ በርካታ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ውሰጥ የመድኃኒት ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ (እስቶክ ካርድ) መዝገብ ያልተቋመ መሆኑና ምዝገባ የማይከናውን መሆኑ፤

4. <u>የአላቂና ቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- በግምጃ ቤቱ በድምሩ ብር 2,350.00 የሚያወጣ ከአንበሳ ጫማ ፋብሪካ የተገዛ 4 አጭርና 1 ረጅም የወንድ ቆዳ ጫማ ያለአገልግሎት ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ከ 570 በላይ የሚሆኑ የወንድ ሸራ ጫማዎች ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ ብዛት ያላቸው በኢትዮጵያ ህጻናት አንባ ስም የታተሙ ደረሰኞች ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለ መሆኑ፤

5. <u>የተማሪዎች ወፍጮ ቤት</u>፤

- በወፍጮ ቤቱ ውስጥ ሁለት የኮሌጁ ሳይክሎች ለበርካታ ዓመታት ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በወፍጮ ቤቱ ከ30 ጆንያ በላይ የሚሆኑ ደረሰኞች ከ20 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በወፍጮ ቤቱ ከ25 ማዳበሪያ በላይ የሚሆኑ የማያገለግሉ መጽሐፍቶች ከ20 ዓመት በላይ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በወፍጮ ቤቱ የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ የሌለ መሆኑ፣

6. <u>የአብጃታ ካምፓስ የተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- በግምጃ ቤቱ 5 ፍሪጅ፣ 15 የእሳት አደጋ መከላከያ፣ 3 ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ 1 የወርቅ ሚዛን፣ 1 ዲፕ ፍሪጅእና 103 የመኪና ጎማ ያለ አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ የኮሌጁ ንብረት የሆኑ ከ100 በላይ የሚሆኑ ጎማዎችና ብረታ ብረቶች ከኦሮሚያ ፖሊስ ኮሌጅ ሰልጣኞች ንብረት ጋር ተቀላቅሎ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤

7. <u>የአሳማ እርባታን በተመለከተ</u>፤

- 16 ማዳበሪያ የተመረዘ የአሳማ መኖ ካልተበላሸ የአሳማ መኖ ጋር በአንድ ላይ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤
- በአሳማ መኖ ማቀነባበሪያ ውስጥ የሚሰሩት ባለሙያ ባለመሆናቸው ምክንያት በተሰራ ስህተት የተመረዘ መኖ በመመገባቸው ከ70 በላይ የሚሆኑ አሳማዎች መሞታቸው፤

8. በዘርዓይድረስ ንብ እርባታ ከ27 በላይ የሚሆኑ የንብ ቀፎዎች ቢኖሩም ቀፎዎቹ በአግባቡ አለመያዛቸውና ቦታውም ለንቦቹ አመቺ አለመሆኑ፤

የታወቀ ሲሆን ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም በአብዛኛዎቹ ላይ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

2.1.4. <u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. <u>በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት</u>

ጊዜ ያለፈባቸውና አገልግሎት የማይሰጡ 12 ኦቨርሄድ ፕሮጀክተሮች፣ 12 ፕሪንተሮች፣ አንድ የቡና ማሽን እና በርካታ ጄነራል ጆርናል ፓዶች ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

2. <u>በኮሌጁ ክሊኒክ</u>

በርካታ የህክምና ዕቃዎች ቢኖሩም በሰለጠነ የሰው ኃይል ምክንያት ያለአገልግሎት ታሽጎባቸው የሚገኙ መሆኑ፤ (በ2006 እና

በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በድጋሚ ተገኝቷል)

3. ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው በመዝገብ ላይ (በእስቶክ ካርድ) ላይ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
4. በኮሌጁ የምርት ግምጃ ቤት የእህል ማድረቂያ ማሽን ለረጅም አመታት ያለ አገልግሎት በግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤
5. በእርዳታ እና በስጦታ የገቡ እቃዎች ዋጋ ያልተተመነላቸው መሆኑ፤
6. በኮሌጁ ያሉት ከብቶች ከኮሌጁ ውጪ ካሉት ከብቶች ጋር የሚገናኙ መሆኑ፤

2.1.5. <u>በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. የጀኔሬተር ማስቀመጫ ቤቶች ግድግዳቸው እና ጣሪያቸው እየተሰነጠቀ የሚገኝ መሆኑ፤
2. የኮሌጁ ላይብረሪ ጣሪያ የሚያፈስ መሆኑ፤
3. መምህራንና ሰራተኞች መኖሪያ ህንጻዎች ላይ የተገጠመው መቀዝቀዣ (ኤሲ) ሁሉም በአብዛኛው የማይሰራ መሆኑ፤
4. በሁሉም ግምጃ ቤቶች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ንብረቶች ተቀላቅለው የተቀመጡ ከመሆናቸውም በላይ በዓይነት ያልተለዩና ለቆጠራ በማያመች መልኩ አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው የሚገኙ መሆኑ፤
5. ሊወገዱ የሚገባቸው 13 ጠርሙስ ሰልፈሪክ እና 10 ጠርሙስ ሃይድክሎሪክ አሲድ የሚገኝ መሆኑ፤
6. በነዳጅና ቅባት ግምጃ ቤት ውስጥ የእሳት ማጥፊያ የሌለ መሆኑ፤
7. በኮሌጁ እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም በተሟላ መልኩ ምዝገባው ያልተካሄደ መሆኑ፤ (ለምሳሌ የተማሪዎች ካፍቴሪያ የምግብ ጥሬ እቃ ግምጃ ቤት ሙሉ በሙሉ፣ የተማሪዎች ክልኒክ የፋርማሲ ዕቃዎችና ደስታ ወረቀት ይጠቀሳሉ)
8. አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ንብረቶች (ወደ ዘጠና የሚጠጉ የማያገለግሉ የመኪና ጎማዎች እንዲሁም 25 ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ 30

የሚሆኑ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ 34 ዲስክቶፕ ኮምፒዩተሮች ከነፕሮሰሰሩና ከኬብሎቹ ጋር) እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤

9. በውድ ዋጋ የተገዙ ሁለት ጄኒሬተሮች ከህንጻው ግንባታ ጋር በሰንሻይን ድርጅት የተተከሉ ቢሆንም ከመጡበት ቀን ጀምሮ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፤
10. ወደ ስድስት የሚሆኑ ጄኒሬተሮች በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
11. የቋሚና አላቂ እቃዎች ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤
12. የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድና መዝገብ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ መሆኑ፤
13. በርዳታና በስጦታ የመጡ እቃዎች ዋጋ ያልተተመነላቸው መሆኑ፣
14. ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም በቋሚ ንብረት መጠየቂያና ወጪ ማድረጊያ ደረሰኝ ቁጥር 000245 በአቶ ዳኛቸው መኩሪያ የወጣው ቶሺባ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር የጠፋ ሲሆን፣ ኮሌጁ ንብረቱን እንዲከፍሉ ለግለሰቡ ደብዳቤ የጻፈላቸው ቢሆንም ግለሰቡ የንብረቱን ዋጋ መክፈል አለመጀመራቸው፤
15. አቶ ጌታሁን ግርማ ህዳር 28 ቀን 2005 ዓ.ም በንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር 000268 ዲጂታል ካሜራ እንዲሁም መጋቢት 23 ቀን 2003 ዓ.ም በንብረት ወጪ ደረሰኝ ቁጥር 000134 ላፕቶፕ ኮምፒተር በስማቸው ያወጡ ሲሆን፣ ከሥራቸው በ2006 በጀት ዓመት ሲለቁ ያወጡትን ካሜራ ተመላሽ ለማድረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

የታወቀ ሲሆን ከላይ ከተራ ቁጥር 1.7 እስከ ተራ ቁጥር 1.15 በተመለከቱት ግኝቶች ላይ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በ2007 በጀት ዓመት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

2.1.6. <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሠረት የስቶክ መዛግብቶችን የመያዝና ስቶክ የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሠራተኛ መስጠት እንደሌለባቸው የተመለከተ ቢሆንም

በኮሌጁ በሁሉም የንብረት ዕቃ ግምጃ ቤቶች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀትና የስቶክ ምዝገባ የማከናወን የንብረት መጠበቅ ኃላፊነቶች ሥራ በንብረት ግምጃ ቤቶቹ ሰራተኞች የሚከናወን መሆኑ፤

2. ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በመምህራን ቤት ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች በቆጠራ ያልተካተተ መሆኑ በተጨማሪም ቆጠራው በመዝገብ ላይ (በእስቶክ ካርድ) ላይ ከተመለከተውና ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤

3. የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ዕቃዎችን ለመለየት በማያስችል ሁኔታ ተደባልቀው የተቀመጡ መሆኑ፤

4. በእርዳታ እና በስጦታ የሚገቡ እቃዎች ዋጋ ያልተተመንላቸው መሆኑ፤

5. የእስቶክ ምዝገባ ወቅታዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

6. ለቋሚ እቃዎች መለያ ታግ ቁጥር ያልተለጠፈላቸው መሆኑ፤

7. የኮሌጁ የግቢው አጥር በአግባቡ ያልተከለለ እና አብዛኛው ክልሉ ክፍት መሆኑ፤

8. ብዛቱ 39 የሚሆን HP, ብዛቱ 72 Canaan ፣ ብዛቱ 28 Brother TNO4M ብዛቱ 12 HP 610A እና ብዛቱ 21 Ink toners 92A በጠቅላላው 172 አገልግሎት መስጠት የማይችል በተለያየ ጊዜ ከእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር በስጦታ የመጣ የፕሪንተር ቀለም ካሉት ኮምፒውተሮች ጋር የማይገጥም በስቶር ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ እና ባገለገሉ እቃዎች ማስቀመጫ ግምጃ ቤት ደግሞ ከ200 በላይ የሚሆን የተለያየ ቁጥር ያላቸው አሮጌ ጎማ፣ አምስት ፐሮጀክተር፣ በርካታ ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች በተለያየ ቦታ፣ ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ ሁለት ፍሪጅ፣ ብዛት 25 የሚሆኑ ፋይል ካቢኔት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

9. ከአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በስጦታ መልክ የመጡ ስድስት ሳጥን የታሸጉ የላብራቶሪ እቃዎች ከሶስት አመት በላይ ሳይከፈቱና አገልግሎት ላይ ሳይውሉ የሚገኙ መሆኑ፤

ታውቋል። በአብዛኛዎቹ ላይ ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ወቅትም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ አለመወሰዱ፤

2.2. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

2.2.1. <u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ</u>

1. የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ ያልቀረበላቸው ስድስት ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፣

   (የሰሌዳ ቁጥራቸውም፡- 4-03788, 4-08798, 4-08792, 4-31278, 4-06526, እና 4-04633)

2. አገልግሎት የማይሰጡ 22 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፣

2.2.2. <u>በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. የሰሌዳ ቁጥር ኮድ UN-0965 ቶዮታ አውቶሞቢል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩ የ "UN Development Program" ሥም መሆኑ፤
2. የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4 ኢት-05421 እና ኮድ 4 ኢት-10149 ቶዮታ ሎንግ ቤዝ አውቶሞቢል ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤
3. አስር ሊብሬ የሌላቸው ሞተር ሳይክሎች መኖራቸው፤
4. ብዛታቸው 22 የሆኑ ቦክሰር ሞተር ሳይክሎች ሊብሬና የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤

2.2.3. <u>በአርጳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. መሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝግቦ ለመያዝ እንደደረጃቸው የተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው

በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸው የሚደነግግ ቢሆንም ሁለት መኪናዎች ታርጋ ቁጥራቸው ኢ.ት. 00703፣ እና ኢ.ት 4-01127፣ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤

2. የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊብሬ ያልቀረበላቸው አምስት ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤ (የሰሌዳ ቁጥር ኢ.ት 4-02480፣ ኢ.ት 4-4376 እና ኢ.ት 4-4377 እንዲሁም አንድ ባጃጅ እና አንድ ትራክተር ሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ)
3. አገልግሎት የማይሰጡ 6 ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፤ (የሰሌዳ ቁጥራቸውም፡- ኢ.ት 4-24817፣ ኢ.ት 4-24818፣ ኢ.ት 4-01452 ኢ.ት 4-13390፣ ኢ.ት 4-0788 እና ኢ.ት 4-0744)
4. በኮሌጁ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው ሰባት ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤

የታወቀ ሲሆን፣ በአብዛኛዎቹ ግኝቶች ላይ በ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማስተካከያ በተሟላ ሁኔታ እርምጃ አለመወሰዱ፤

2.2.4. <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

1. መሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተልና መዝግቦ ለመያዝ እንደደረጃቸው የተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸው የሚደነግግ ቢሆንም በኮሌጁ ይህ የማይደረግ መሆኑ፤ (ለምሳሌ ያህል የጭነት አይሱዙ ታርጋ ቁጥር 4-03042 እና ቤላሩስ ትራክተር)

2. ለበላይ ኃላፊዎች እና ለኃላፊዎች ከሚመደቡ ተሽከርካሪዎች በስተቀር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀው የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪሎ ሜትር መጠን ጋር እየተመዘገበ ተገቢዉ ሪፖርት በየወሩ የማይቀርብ መሆኑ፣

3. አራት ሞተር ሳይክሎች (የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-0786 ኢ.ት፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-0354 ኢ.ት፣ የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 4-0353 እና የሰሌዳ

ቁጥር ኮድ 4-1812) በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት ቆመው የሚገኙ መሆኑ፣

4. ኮሌጁ የሚጠቀምበት ቤላሩስ ትራክተር ሰሌዳ ቁጥርና ሊብሬ የሌለው መሆኑ፣

2.3. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ሰራተኞች ሲለቁ በሥራ ላይ በነበሩበት ወቅት ይገለገሉበት የነበረውን ቋሚ ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ የሚያደርጉ መሆኑን ለማጣራት በናሙና የተወሰኑ ሰራተኞች ፋይል ኦዲት ሲደረግ፡-

2.3.1. <u>በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ</u>

1. ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት የተዛወሩ አምስት ሰራተኞች የተረከቡትን ቋሚ እቃ ያስረከቡ ወይም ወደ ሌላ ሰው ያስተላለፉ ቢሆንም ንብረቶቹ ከዩዘር ካርዳቸው ላይ ያልተሰረዙ መሆኑ፤

2. በጡረታ ከመሥሪያ ቤቱ ለተሰናበቱ አንድ ሰራተኛ መልቀቂያ (ክሊራንስ) የተሰጣቸው ቢሆንም በእጃቸው ይገኝ የነበረው ንብረት ስለመመለሳቸው ማስረጃ ያልቀረበ እና ከዩዘር ካርዳቸው ላይም ያልተዘረዘ መሆኑ፤

3. አንድ ሰራተኛ መሥሪያ ቤቱን በገዛ ፍቃዳቸው ሲለቁ መልቀቂያ (ክሊራንስ) የተሰጣቸው ቢሆንም በእጃቸው ይገኝ የነበረውን ላፕቶፕ ኮምፒተር ስለመመለሳቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

2.3.2. <u>በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>

1. ወደ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር የተዛወሩ ሁለት ሰራተኞች የተረከቡትን ግምታቸው ብር 71,663.57 የሆኑ ቋሚ እቃዎችን ያስረከቡ ወይም ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፋቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

2. በጡረታ ከማስተባበሪያው የተሰናበቱ አንድ ሰራተኛ የተረከቡትን ግምታቸው ብር 96,043.58 የሆኑ ቋሚ እቃዎችን ያስረከቡ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

2.4. በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል። ሆኖም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን በተጠሪ ተቋማቱ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ስለሁኔታው ቀደም ባሉት ዓመታት በተደረጉ ኦዲት ወቅት በተደጋገሚ የተገለጸ ቢሆንም ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፤

2.5. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ያለው የሰው ሀብት አስተዳደር የእድገት የቅጥርና የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተገቢነትን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ተጠሪ ተቋማቱ በዕቅድ የያዛቸውን ተግባራት በአግባቡ ለመፈጸም ይችል ዘንድ ክፍት የሥራ መደቦችን በሰው ኃይል መሙላት እንዳለበት ይታመናል። ሆኖም፡-

1. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 1796 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 938 ሲሆን 858 (47.7%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤

2. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በውድ ዋጋ ተገዝቶ የተተከለው አቴንዳንስ (የአሻራ ሰዓት መቆጣጠሪያ) ሰራተኛው በአግባቡ የማይጠቀምበት መሆኑ፤

3. የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በመዋቅር ከተፈቀዱለት 1001 የሥራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 762 ሲሆን 239 (23.87 %) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤

4. የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በመዋቅር ከተፈቀደለት 791 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 647 ሲሆን 144 (18%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤

5. **የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በመዋቅር ከተፈቀደለት 430 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው** 249 **ሲሆን** 181 **(42%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤**

6. **የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ በመዋቅር ከተፈቀደለት 498 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው** 310 **ሲሆን** 188 **(38%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤**

2.6. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱንና የተጠሪ ተቋማቱን ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

2.6.1. <u>በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት</u>

1. **ማስተባበሪያው የቅጥር መስፈርቶች ሳይሟሉ አንድ ጀርመናዊ የቴክኒክ ባለሙያ ከኦክቶበር** 2015 **እስከ ማርች** 2016 **ዓ.ም ድረስ በኮንትራት በየወሩ በብር** 3,727.50 **ቅጥር የፈጸመ ከመሆኑም በተጨማሪ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር** 286/2002 **መሰረት ተቀጣሪው ታክስ እንዲከፍሉ ያልተደረገ ሲሆን፣ በፕሮጀክት ሥምምነቱ መሰረት የቴክኒክ ባለሙያ መመደብ ያለበት የጀርመን መንግሥት ለመሆኑ በሁለቱ ሀገሮች ሥምምነት ላይ የተቀመጠ ሆኖ ሳለ ቅጥሩ በኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሸፈን መደረጉና አሁንም ክፍያው ቀደም ሲል በነበረው አካሄድ የቀጠለ መሆኑ፤**

2. **ለጎዴ ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ ከ**1996 **ዓ.ም በፊት ጀምሮ ለሥራ ማስኬጃ ተልኮ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሳብ በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ሂሳቡ እንዲወራረድ ሲደረግ፡-**

   2.1. ብር 22,805.00 **የ**2007 **በጀት አመት አካል ሆኖ በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም በወጪ እንዲመዘገቡ ለተደረጉት ሂሳቦች የወጪ ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑ፤**

2.2. ብር 181,760.00 የተለያዩ ግዢዎች ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ያልቀረበላቸው መሆኑ፤

2.6.2. በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

1. ንብረት

- ☞ አገልግሎት የማይሰጡ ሃያ ስድስት (26) ፍሪጆች፣ አንድ የውሃ ሞተር ፓምፕ፣ ሁለት ጄነሬተሮች፣ ወንበሮች፣ በርካታ ኮምፒዩተሮች፣ ታይፕ ራይተር፣ ፕሪንተሮች እንዲሁም የፎቶ ኮፒ ማሽኖች በስቶር ውስጥ ያለአገልግለት የሚገኝ መሆኑ፤
- ☞ የኮሌጁ ላይብረሪ እየፈራረሰ መሆኑ፤
- ☞ በኮሌጁ ያሉት ከብቶች ከኮሌጁ ውጪ ካሉት ከብቶች ጋር የሚገናኙ መሆኑ፤

2. ተሽከርካሪ

- ☞ ሁለት ሞተር ሳይክሎች (የሰሌዳ ቁጥር 4-0075 እና 4-0375) ሊቢሬ የሌላቸው መሆኑ፤
- ☞ በከባድ ብልሽት ከአምስት እስከ ስምንት ዓመት ድረስ የቆሙ ሰባት ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤

2.6.3. በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

1. በኮሌጁ ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉ መሰረት የተፈጸመ እና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያን ተከትሎ የተመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኮሌጁ ከአፈወርቅ ግደይ ጋር ባደረገው ሥምምነት መሰረት ለቢሮ ህንጻ እና ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የተፈጸሙ ክፍያዎች ኦዲት ሲደረጉ፡-

- ☞ ብር **333,093.65** በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣
- ☞ ብር **25,444.35** ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ፣
- ☞ ብር **633,083.09** ተቀንሶ ያልተመዘገበና ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣

- ☞ በተጠቀሱት ምክንያቶች ብር 325,433.79 ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣
- ☞ አፈወርቅ ግደይ ህንጻ ሥራ ተቋራጭ ከግንቦት 16/2005 ጀምሮ ባሉት 360 ካላንደር ቀን ውስጥ ማለቅ እንዳለበት በውሉ ላይ የተመለከተ ቢሆንም ሥራው ከ840 ቀን (ለሁለት ዓመት ከሶስት ወር) በላይ የዘገየ መሆኑ፤

2. በ2006 በጀት ዓመት ለማስተባበሪያው ተልኮ የተወራረደው የ2005 በጀት አመት የወጪ ሂሳብ ብር 99,883.05 በ2006 በጀት ዓመትም በኮሌጁ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

ተገልጾ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በጀት ዓመት ወቅትም ግኝቶቹ ላይ ማስተካከያ ሳይደረግ ባሉበት ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ፤

2.6.4. <u>በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ</u>

1. በተሽከርካሪዎቹ ሁለቱም የፊት በሮች ጎን ላይ የኮሌጁን ስም የሚያመለክት መለያ ወይም አርማ ያልተለጠፈ መሆኑ፤
2. አንድ ባልትራ ትራክተር በኮሌጁ ግቢ ውስጥ ብልሽት ምክንያት ከአንድ አመት በላይ ያአገልግሎት ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀበት ቆሞ የሚገኙ መሆኑ፤
3. ላንድሮቨር ታርጋ ቁጥር 21350 ኢ.አ እንዲሁም አራት ሞተር ሳይክሎች ታርጋ ቁጥራቸው 0197, 0198, 0199, 5232 ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ፤
4. ላንድሮቨር፣ ሚትስቡሽ፣ ጃጓር የታርጋ ቁጥር 21350 ኢ.አ፣ 24593 ኢ.አ እና 27524 ኢ.አ እንዲሁም የተወሰነ ክፍላቸው የቀረ ሁለት ትራክተሮች ከ5 አመት በላይ ሳይወገዱ በሰርቶ ማሳያ ግቢ ውስጥ ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኙ መሆኑ፤
5. በኮሌጁ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ያልተዘጋጀላቸው 6 መኪኖች የሚገኙ መሆኑ፤
6. ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም በተዘጋጀው የሳጥን ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0827649 ወ/ት ዘውዴ ግርማ ነሀሴ 23 ቀን

2006 ዓ.ም በጸፉት ደብዳቤ መሰረት በሰራተኛና አስተዳደር ሪከርድና ማህደር ዋና ክፍል ውስጥ የተለያዩ ደብዳቤና እንዲሁም የደረጃ እድገት፣ ቅጥርና፣ በተደራቢነት የተለያዩ ክፍሎችንና የንብረት ቆጠራ እንዲሁም በምሽት ጭምር እንደሚሰሩ ጠቅሰው ለዚህም የማበረታቻ ክፍያ እንዲከፈላቸው በጠየቁት መሰረት ተጠቃሽዋ ናዝሬት ለስራ ጉዳይ እንደሄዱ በማስመሰል የአስር ቀን ዉሎ አበል ብር 1250.00 እንዲሁም የትራንስፖርት አበል ብር 300.00 በድምሩ ብር 1,550.00 እንዲከፈላቸው የተደረገ መሆኑ፤

7. በናሙና ከተመረጡት ሰራተኞች ውስጥ 85 የጥበቃ ሠራተኞችና 1 ገንዘብ ያዥ ዋስትና (ተያዥ) እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ፤

2.6.5. <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ</u>

1. ኮሌጁ ከሰበሰበው የተጨማሪና እሴት ታክስ ብር 538,154.23 ውስጥ ብር 308,154.23 እንዲሁም ግዥ ሲፈጽም ተቀናሽ የተደረገው የቅድሚያ ግብር ብር 118,497.26 ውስጥ ብር 86,309.74 ለሚመለከተው የገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት ገቢ ከመደረጉ በፊት ወዲያዉኑ ተቀናሽ እንደተደረገ ምዝገባ እንዲከናወን ያልተደረገና ክፍያው ለመፈጸሙም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

2. በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ማስረጃ ካልቀረበለት የወጪ ሂሳቦች ብር 1,623,558.73 ውስጥ ለብር 886,996.88 ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን፣ ለቀሪው ለብር 736,561.85 በዚህ በጀት አመትም የወጪ ሂሳብ ማስረጃዎች ሊቀርብላቸው ያልቻለ መሆኑ፤

3. ኮሌጁ የመምሕራን መኖሪያ ቤት ግንባታ እስክንድር ታዬ የህንጻ ሥራ ተቋራጭ እንዲያከናውን በፈጸመው ውል የተፈጸሙ ክፍያዎችና የአመዘጋገብ ሥርዓቱ መመሪያውን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ብር 49,047.43 በወጪ ያልተመዘገበ ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 312,068.34 በክፍያ ሰርተፊኬቱ ላይ ተቀንሶ ቢታይም ክፍያው ሲፈጸም ያልተቀነሰና ያልተመዘገበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ፣
- ብር 49,047.43 ተቀንሶ ያልተመዘገበ የመያዣ ሂሳብ መኖሩ፣

- ብር 18,724.11 ከክፍያው ላይ እንዲቀነስ ቢታዘዝም ክፍያው ሲፈጸም ያልተቀነሰና ያልተመዘገበ የቅድሚያ ግብር ሂሳብ መኖሩ፣
- ብር 330,792.34 በብልጫ የተከፈለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ መኖሩ፣

ተገልጾ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያት የተሰጠ ቢሆንም በተጠቀሰው ግኝት ላይ አስፈላጊው እርምጃ አለመወሰዱ ታውቋል፡፡

2.7. አንድ ተቋም ምንም ዓይነት የተግባር ስራ ከመጀመሩ በፊት ሊሰራቸው የሚገቡትን ስራዎችና ሊደርስበት የሚያስበውን ደረጃ ማቀድና የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ስራ መጀመር እንዳለበት ይታወቃል። ሆኖም የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የተሰጠውን ተልኮ በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል የስትራቴጂክ እቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ፤

2.8. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ለሚሰቱት የትምህርት ዕድል የግዴታ ውል የሚያስገቡ፣ ዋስ የሚያስጠሩ መሆኑን እና የትምህርት ዕድል ያገኙት መምህራን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ግዴታቸውን የሚወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

2.8.1. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በመምህርነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ የነበሩ 4 (አራት) መምህራን፣

2.8.2. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በመምህርነት ተቀጥረው ሲያገለግሉ የነበሩ 8 (ስምንት) መምህራን፣

በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲማሩ የተፈቀደላቸውና ከኮሌጁም ጋር ውል የፈጸሙ ሲሆን፣ በገቡት ውል መሰረት ህጉን ካፈረሱ የወጪው 15 በመቶ ታክሎበት ለመክፈል ወይም ተመጣጣኝ አገልግሎት ለመስጠት ውል የገቡ እና ዋስትና ያስያዙ ቢሆንም መምህራኖቹ የገቡትን ግዴታ ሳይወጡ ሥራቸውን ለቀዋል። ሆኖም ግለሰቦቹ በገቡት ግዴታ መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም አስፈላጊው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

2.9. በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ግቢ ውስጥ ያሉት ቤቶች ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አንድ

የዞኑ አስተዳደሪ እና የጀርመን ዜግነት ያላቸው የቤንች ቋንቋ ላይ ጥናት የምያደርጉ ሴት በግቢ ውስጥ ቤት ተሰጥቷቸው ለረጅም አመታት እየኖሩበት የሚገኙ መሆኑ፤

2.10. በፋይናንስ አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና በፋይናንስ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 970/2008 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 47/2009 መሰረት እንዲሁም በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት እያንዳንዱ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የዉስጥ ኦዲት ክፍል በየሩብ አመቱ የመሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራርና ሠራተኞች ኃላፊነታቸዉን በብቃት መወጣት እንዲችሉ በተዘረጋዉ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በሥራ ላይ ባሉት ህጎችና የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት ስራዎች መከናወናቸዉን ኦዲት እያደረገ በመመሪያዉ ላይ በተቀመጡት ግዜ ዉስጥ ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊና ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት የሚያደርግ መሆኑን በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና በተጠሪ ተቋማቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

2.10.1. <u>የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት</u>

1. ለዳይሬክቶሬቱ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 22 ሲሆን አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የሰው ኃይል 6 ብቻ መሆኑ፣
2. የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ሥር የሚገኙ ኮሌጆች የውስጥ ኦዲት ክፍሎች ዓመታዊ የኦዲት ሥራ እቅዳቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲያቀርቡ የማያደርግ እና የኦዲት ዕቅድ ሥራቸውን የማይገመግም መሆኑ፣
3. ዳይሬክቶሬቱ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ሥር የሚገኙ ኮሌጆች የውስጥ ኦዲት ክፍሎች የፈሰስ ሪፖርታቸውን እንዲያቀርቡ በማድረግ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፈሰስ ሪፖርቱ ጋር እንዲጠቃለል የሚያደርግ መሆኑ ሲጣራ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀው የፈሰስ ሪፖርት የገዋኔንና የሚዛንን ግ/ቴ/ሙ/ት/ሥ/ ኮሌጆችን ያላካተተ መሆኑ፣

4. በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ሥር የሚገኙ ኮሌጆች የውስጥ ኦዲት ክፍሎች የየሩብ ዓመት ሪፖርታቸውን ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት እንዲያቀርቡ ክትትል የማይደረግ መሆኑ፣

5. ዳይሬክቶሬቱ በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ሥር ከሚገኙ ኮሌጆች በናሙና በመመረጥና ዓመታዊ እቅድ በመያዝ የኦዲት ሥራ የማያከናውን መሆኑ፤

2.10.2. የገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

1. ለውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 3 ሲሆን አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የሰው ኃይል 1 ብቻ መሆኑ፣
2. የውስጥ ኦዲቱ ዓመታዊ የሥራ እቅድ የሌለው መሆኑ፣
3. የውስጥ ኦዲት ሰራተኛው የሂሳብ ሥራ ዝግጅትን ደርቦ የሚሰራ መሆኑ፣
4. የውስጥ ኦዲቱ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሰረት የየሩብ ዓመቱ ሂሳብ ኦዲት ያላደረገና ሪፖርት ለኮሌጁ የበላይ ኃላፊና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ኦዲት ዳይሬክቶሬት ያልቀረበ መሆኑ፣

የታወቀ ሲሆን የውስጥ ኦዲቱን በተመለከተ በ2007 ኦዲት ወቅትም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ምንም ዓይነት የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰዱ፤

5. በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 35 ተራ ቁጥር 3 መሰረት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረግ ሂሳብ ለ/ ላይ ከመንግስት ግምጃ ቤት የገንዘብ ምንጭ ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃ በቅድሚያ በሰነድ ተከፍሎ ሳይወራረድ በየዓመቱ መጨረሻ በሣጥን ከተቆጠረው ውስጥ ክፍያው በበጀት ዓመቱ የተፈጸመና አገልግሎቱ በተከታዩ በጀት አመት ውስጥ የሚሰጥ አላቂ ንብረት ሂሳብ በፈሰስ ሂሳብ ሊመዘገብና ለገ/ኢ/ት/ሚ ፈሰስ ሊደረግ እንደሚገባ ያመለክታል። ይሁን እንጂ የኮሌጁ የውስጥ ኦዲት ክፍል በ2009 በጀት አመት መጨረሻ የጥሬ ገንዘብና የአላቂ እቃ የፈሰስ ሪፖርት ያላዘጋጀ መሆኑ፤

2.10.3. የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የውስጥ ኦዲት ክፍሉ በመዋቅር የተፈቀደው የሰው ኃይል 3 ሲሆን አሁን በስራ ላይ የሚገኝ ሰራተኛ የሌለ በመሆኑ ምክንያት በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት የየሩብ ዓመቱን ሂሳብ ኦዲት ያላደረገና የፌሰስ ሪፖርትም ያላዘጋጀ መሆኑ፤

ታውቋል።

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

ግንቦት 2010 ዓ.ም